*የሰ/መ/ቁ. 60353*

*ግንቦት 04 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ባልቻ ወ/ፃድቅ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ግርማ ቀለታ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ቃረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ያቀረበ ነው አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት የጥበቅና ግልጋሎት አሰጣጥን በሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የነበረኝን የፍታብሔር ክርክር ለመከታተልና ጉዳዩን እስከሰበር ችሎት ድረስ እኔን በመወከል ሊከራከሩልኝ ከተጠሪ ጋር ውል ተዋውለናል፡፡ ከሳሽ በውል ከተስማማነው ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ውስጥ ብር 1,000 /አንድ ሺ ብር/ ለተከሳሽ ከፍያለሁ፡፡ ተከሳሽ ተገቢውን የጥብቅና አገልግሎት ያልሰጡኝ በመሆኑ የከፈልኩትን ገንዘብ ከነኪሣራው እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ የማህበራዊ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የተዋዋለው በአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለመከራከር እንጂ በይግባኝና በሰበር ለመከራከር አይደለም በማለት የማህበራዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለከተማው ሰበር ችሎት አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ጋር ያደረግሁት የጥብቅና አገልግሎት ውል ተጠሪ እኔ ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር ባለኝ የፍታብሔር ክርክር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ሊቆሙልኝ መሆኑ በውሉ ተገልፆ እያለ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ ያየው የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት ውሉ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር የተደረገነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ በአዲስ አበባ

የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የጥብቅና ግልጋሎት ለመስጠት የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረቡ የማይጠቅማቸው መሆኑን መክሬአቸዋለሁ፡፡ አመልካች ከሙያ አንፃር የማያዋጣውንና የማላምንበትን ጉዳይ ይግባኝ ካላቀረብክ በማለት ያቀረቡት ክስ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገው የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነት "እኔ ውል ሰጭ ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስላለኝ የቦታ ክርክር ጉዳይ ውል ተቀባይ ባላቸው የጥብቅና ሙያ ጉዳዬን እስከ መጨረሻ ድረስ ሊከራከርልኝ ለዚህ አገልግሎታቸው ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ልከፍላቸው የተስማማን ሲሆን" በሚል መንገድ በተራ ቁጥር 1 የአመልካችን ግዴታ የሚገልፅ ሲሆን በተራ ቁጥር 2 "እኔም ውል ተቀባይ በተራ ቁጥር 1 ላይ በተገለፀው መሠረት የውል ሰጭው ጉዳይ እስከመጨረሻ ድረስ ልከራከርላቸው ተስማምተን በቅደሚያ ብር /አንድ ሺ ብር/ ተቀብያለሁ" በሚል መንገድ የተጠሪን ግዴታ የሚገልጽ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በተደረገው ውል ውስጥ " እስከመጨረሻ ድረስ ሊከራከሩልኝ" የሚለውና "እስከ መጨረሻ ድረስ ልከራከርላቸው" የሚለው ቃል ተጠሪ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር የውል ግዴታ እንደገቡ በማድረግ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1732 እና የጥብቅና አገልግሎት በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀፅ 8/2/ የተደነገገውን ያላገናዘበና የአተረጓጎም ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ "እስከ መጨረሻ ድረስ" ልከራከርላቸው በማለት ተጠሪ የገቡት ውል ይዘት አመልካች ከሙያ አንፃር የሚያዋጣ ከሆነ ይግባኝ አቅርቦ የመከራከርና በሰበር አቤቱታ አቅርቦ መከራከረን የሚጨምር በመሆኑ በዚህ በኩል የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው በሰበር ችሎት የሰጡት ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም ተጠሪ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር ነው በጥብቅና አገልግሎት ውሉ የተስማማሁት በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ አልተቀበልነውም፡፡

የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን ውል ሲተረጉሙ ስህተት የሰራ ሲሆን ተጠሪ ያቀረበው ሁለተኛ መከራከሪያ ስንመለከተው ፍርድ ቤቶቹ የደረሱበትን መደምደሚያ የሚያስለውጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ከሙያ አንፃር አመልካች ከህግ አንፃር ማድረግ የሚገባቸውን የማስረዳትና ግልፅ የማድረግና የማማከር ግዴታና አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ክስና ክርክር ያለማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 28 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በአመልካችና በወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ መካከል በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር የቦታ ይዞታ ክርክር ሲሆን በጉዳዩ አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበው ነበር፡፡ በክርክሩ ሂደት ክርክር የተነሳበት ቦታ የማናቸው ይዞታ እንደሆነ አጣርቶ እንዲገልፅ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳዳር ተጠይቆ ተከሳሽ ወ/ሮ እታገኘሁ የአመልካችን ቦታ አልፎ እንዳልያዘ እና በተቃራኒው አመልካች የወ/ሮ እታገኘሁን ህጋዊ ይዞታ አልፎ የያዘ መሆኑን በማረጋገጡ የአመልካች ክስ ውድቅ መሆኑን የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00076 ሀምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ

ይግባኝ ባይ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ከሙያ አንፃር እንደማያዋጣ የምክር አገልግሎት ከሰጠ ለአመልካች የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡ አመልካች የተጠሪን ምክር ወደጎን በመተው ይግባኝ አቅርቦ ይግባኙ የተሠረዘበት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ተገቢ የሆነ የሙያ ግልጋሎትና ምክር ለአመልካች የሰጠ በመሆኑ በውጤት ደረጃ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

ቅ/መ